# ለእግዚአብሔር ፍቅር

“…እኔ የሚረባህን ነገር የማስተምርህ በምትሄድባትም መንገድ የምመራህ አምላክህ እግዚአብሔር ነኝ።” (ኢሳ 48÷17)



God's Love, P.O.Box 6734, Lee's Summit, MO 64064 / E-mail:- mtizazu@hotmail.com / Ph/Fax 816 – 246 - 9395



ነሐሴ 1994 -- August 2002 “ልጆችሽም ሁሉ ከእግዚአብሔር የተማሩ ይሆናሉ÷ የልጆችሽም ሰላም ብዙ ይሆናል ።” ኢሳ 54÷ 13

አዘጋጅ :- መላኩ ትዕዛዙ


## በትዕግስት ፀጥታ በፀሎት ቆይታ
### መልስ ይመጣል፡ከጌታ

“የያዕቆብ አምላክ ረዳቱ የሆነለትና በአምላኩ በእግዚአብሔር ተስፋ ያደረገ ሰው ደስ ይበለው ምክንያቱም… እርሱ ዘወትር ቃል ኪዳኑን ይጠብቃል ለተጨቆኑት ይፈርዳል፤ ለተራቡት ምግብን ይሰጣል።” (መዝሙረ ዳዊት 146÷5-7 አዲሱ ትርጉም)

“እግዚአብሔርን በመታመን የሚጠባበቁ ግን ኃይላቸውን ያድሳሉ፤እንደ ንስር በክንፍ ይወጣሉ፤ይሮጣሉ÷ አይታክቱም፤ ይሄዳሉ÷ አይደክሙም።” (ኢሳይያስ 40÷31)

በሕይወቱ ዘመን አንድ በተስፋ የሚጠባበቀው ነገር የሌለው ሰው መኖሩ ያጠራጥራል። ተማሪው ትምሕርቱን ለመጨረስ÷የጨረሰውም ሥራ ለማግኘት ÷ በተስፋ ይጠባበቃል። ያላገባው ትዳር ለመያዝ÷ ትዳር የያዘም ልጅ ለመውለድ÷ የወለደው ደግሞ ልጆቹ በመልካም አድገው እንዲደርሱለት በተስፋ ይጠባበቃል። ይህን ጽሑፍ የምታነቡ ጌታ ያደርግልኛል ብላችሁ የምትጠብቁት ነገር ይኖራችኋል። የጥበቃውም ጊዜ ረዝሞ ይሆናል።

ይህ ያለንበት ዘመን÷ ሁሉ ነገር የፈጠነበት ዘመን ነው። ቅጽበታዊ ቡና÷ ቅጽበታዊ ምሣ በፈጣኑ ማይክሮ-ዌቭ ምድጃ÷ ምግብን ብቻ ሳይሆን ረሃቡንም ያፈጠነ ይመስላል ። ከአሥራ ስድስት ዓመት በፊት መንጃ ፈቃዴን ስቀበል በአሜሪካን አውራ ጐዳኖች÷የመንጃ ፍጥነት በሰዓት ሃምሳ አምስት ማይል ነበረ። ያም እንኳ ለጀማሪ ነጂ ያስፈራ ነበረ፤ዛሬ ግን ሰባ ማይል ሕጋዊ የሆኑባቸው ጐዳናዎች በዝተዋል። ከዚያም በላይ መፍጠን እንደቀድሞው አይገርመንም። ምክንያቱም ይህ የችኮላ ዘመን ስለሆነ ነው እንግዲህ:- ምንም እንኳ በትዕግሥት መጠበቅ ቀላል ሆኖ ባያውቅም÷ በስልጣኔ ያፈራነው ጥድፊያና ግብ ግብ የእኛን ዘመን ትዕግሥት የጎደለው አድርጎታል።

ከፍ ሲል እንደ ጠቀስነው ሰው ሁሉ በየትኛውም የሕይወት ዘመኑ÷በተስፋ የሚጠባበቀው ነገር አለው። እግዚአብሔርም ሰውን ያስጠብቃል። ለምሳሌ፡ የያዕቆብን ልጅ የዮሴፍን ታሪክ እንውሰድ :-

ይህ ሰው ከልጅነቱ ጀምሮ የእግዚአብሔር ተስፋ ነበረው፤ ጌታ የገለጠለትን ነገር የሚጠባበቅ ሰው ነበረ። ሆኖም ከሞት አፋፍ አምልጦ በተሸጠበት ሐገር በእግዚአብሔር ፊት ኃጢአት ላለማድረግ÷ በሐሰት ተከሶ÷በግዞት መቆየት ነበረበት። ረዳቱም በቶሎ አልመጣም ነበር። (ኦሪት ዘፍጥረት 39)

በዘፍጥረት ምዕራፍ አርባ እንደምናየው÷ ዮሴፍ የጠጅ አሳላፊዎቹን አለቃና የእንጀራ አበዛዎቹን አለቃ ሕልም በመፍታቱ ምክንያት ከእስራት የመውጣት ተስፋ ነበረው። የጠጅ አሳላፊዎች አለቃ ግን ለሁለት ዓመታት ረሳው። (ኦሪት ዘፍጥረት 41)

ከዚያ በኋላ በድንገት የዮሴፍ ጥበቃው የሚያበቃበት ምክንያት ተፈጠረ። ያም ምክንያት የንጉሡ የፈርዖን ሕልም ማለም ነበር።የንጉሡንም ሕልም የሚፈታ በሐገሩ አልተገኘም። በዚያን ጊዜ በግዞት የነበረው የጠጅ አሳላፊዎቹ አለቃ ሕልሙን ስለ ተረጎመለት ዕብራዊ ስለ ዮሴፍ ተናገረ። “ፈርዖንም ልኮ ዮሴፍን አስጠራ÷ ከግዞት ቤትም አስቸኰሉት፤ እርሱም ተላጨ÷ልብሱንም ለወጠ÷ወደ ፈርዖንም ገባ።” (ዘፍጥረት 41÷14) በዚህ ጊዜ ዮሴፍ ግብጽ ምድር ከገባ እንኳ አሥራ ሦስት ዓመት በተስፋ ታግሷል። እግዚአብሔርን መፍራቱ ታይቷል። ዕምነቱና ትዕግሥቱ ተፈትኖ አልፏል። እንዲህ ማስጠበቁ በዘመናት ሁሉ የታየና ዛሬም ያልተለወጠ የጌታ አምላካችን አሠራር ነው።

## ከዮሴፍ የተሳካ ትዕግስትና ጥበቃ ምን እንማራለን?

### በንቃት መጠበቅ:-

እግዚአብሔር በትዕግሥት እንድንጠብቀው ሲያደርገን በዓላማ ስለ ሆነ ፈቃዱን ለመረዳትና ለመከተል በንቃት መጠበቅ አለብን። አብዛኛው ከፊታችን ለሚጠብቀን ሰልፍ የምናደርገው ዝግጅት የሚከናወነው በማስጠበቁ ወቅት ነው፤ ስለዚህ ጌታን እጠብቃለሁ ብሎ እጆችን አጣጥፎ መቀመጥ የተወደደ ጊዜን ማባከን እንዳይሆን መጠንቀቅ ያስፈልጋል፤ በአጠቃላይ በማስጠበቁ ጊዜ ያለው ሁለት ምርጫ ነው :- አንድም ከመቼውም ይልቅ ወደ እግዚአብሔር እንቀርባለን ወይም ደግሞ ወደ ኋላ እናፈገፍጋለን።

### በመታመን መጠባበቅ:-

“አንተ ግን በምድር ላይ በሰላም እንድትኖር÷ በእግዚአብሔር ታመን፤እርሱም የልብህን ፍላጎት ሁሉ ይሰጥሃል። ሁለንተናህን ለእግዚአብሔር ዐደራ ስጥ፤በእርሱ ታመን፤እርሱም ይረዳሃል።…በትዕግሥት ጸንተህ÷እግዚአብሔር የሚያደርገውን ለማየት ተጠባበቅ፤ …”(መዝሙር 37÷5-7 አ/ትርጉም)

በእግዚአብሔር ለመታመን የሚረዳ እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ንባብ ያለ ጠቃሚ ነገር ከቶ አይገኝም። እኛ ዛሬ የምናልፍበት ሁኔታ ÷ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ÷ ተጽፎ ስለሚገኝ÷ ያንን ማንበብ የዕምነት ኃይል ይሰጣል። እምነት ከመስማት መስማትም ከእግዚአብሔር ቃል ስለ ሆነ÷ ቃሉን በማንበብ እየበረቱ÷ታምኖ መጠባበቅ ተስፋን ለመጨበጥ ይረዳል።

### በትዕግሥት÷በጸጥታ መጠባበቅ:-

“በዕምነትና በትዕግሥትም የተስፋውን ቃል የሚወርሱትን እንድትመስሉ እንጂ ዳተኞች እንዳትሆኑ ÷ ተስፋ እስኪሞላ ድረስ እያንዳዳችሁ ያን ትጋት እስከ መጨረሻ እንድታሳዩ እንለምናለን።”
. (ዕብራ ውያን 6 ÷ 11 - 12)

“እንግዲህ ወንድሞች ሆይ÷ ጌታ እስኪመጣ ድረስ ታገሡ፤ እነሆ÷ ገበሬው የፊተኛውንና የኋላኛውን ዝናብ እስኪቀበል ድረስ እርሱን እየታገሠ የከበረውን የመሬት ፍሬ ይጠባበቃል። እናንተ ደግሞ ታገሡ÷ ልባችሁንም አጽኑ÷የጌታ መምጣት ቀርቦአልና።”
. (ያዕቆብ 5 ÷ 7 - 8)

መጨነቅና መነጫነጭ ጥሩ ያለማመን ምልክቶች ናቸው። እግዚአብሔርንም ያሳዝናሉ። ስለዚህ ጌታ የተናገረውን የሚያደርግ÷በቃሉ ታማኝ÷መልካ ምንም ከማድረግ የማይቆጠብ አምላክ መሆኑን የሚያምን ሰው በትዕግሥትና በጸጥታ መጠባበቅ አለበት።

## አለመታከት:-

. ዘማሪው ታምራት ኃይሌ:- “አይቸኩልም ጌታ ዘግይቶ ይነሣል፤ ግን ማንም አይቀድመው በጊዜው ይደርሳል” ያለውን አስተዋይ መዝሙር እናስታውሳለን። የመዘግየቱ ጉዳይ የሰው ግንዛቤ ሲሆን በጊዜው መድረሱ ግን በዘመናት ውስጥ የተረጋገጠ ነው። ምክንያቱም ጌታ ነገሮችን የሚተልመውና የሚሠራው ከዘላለም አንጻር ስለሆነና÷በእኛ የዘመን አቆጣጠር ተገድዶ መቸኮል ስለ ሌለበት ነው። በተጨማሪ አንድን ሰው በክርስቶስ መልክ ሠርቶ ለመፈጸም የሚያስፈልገውን የዕድገት ደረጃ መዝለል ስለማይፈልግ ነው። በተቀረ ግን መዘግየትም ሆነ መቸኮል ለእርሱ አያስፈልጉትም። ስለዚህ ጌታ ጊዜው ሳይደርስ ወደ ሚቀጥለው ደረጃ የሚወስደን ይመስል “በዕምነት መዋዠቅ” (መናወጥ) ያልተጻፈውንም መከተል÷ተስፋ እንዳያስቆርጠን መጠንቀቅ አለብን።

## የራስን ፀሎት በራስ አለመመለስ:-

እግዚአብሔር የዘገየ ሲመስል ሁለት የተለመዱ ስሕተቶች ማድረግ ይቻላል። አንዱ በጌታ ላይ ማጉረምረም ሲሆን ሌላኛው ደግሞ ከእርሱ መምጣት ያለበትን መልስ በራስ ለመፍጠር መሞከር ነው። ለዚህ ጥሩ ምሳሌ የሚሆነውን የአብርሃምን ታሪክ እንመልከት:-

አብርሃም ጌታን በራዕይ ባነጋገረበት ጊዜ:- “አብራምም፡ ለእኔ ዘር አልሰጠኸኝም፤እነሆም÷በቤቴ የተወለደ ሰው ይወርሰኛል አለ። እነሆም ÷ የእግዚአብሔር ቃል እንዲህ ሲል መጣለት:- ይህ አይወርስህም ነገር ግን ከጉልበትህ የሚወጣው ይወርስሃል ።” ሲል የተስፋ ቃል ሰጠው። (ዘፍጥረት 15÷3-4) ከዚህው ጋር አያይዞ “አብራምም በእግዚአብሔር አመነ ጽድቅም ሆኖ ተቈጠረለት።” ሲል ለአብርሃም የተሰጠውን ምስክርነት መጽሐፍ ያሳየናል (ዘፍጥረት 15÷ 6) ቆይቶ ግን አንድ ችግር ተፈጠረ ። የተስፋው ቃል “ዘገየ”። አሥር÷ ሃያ÷ አልፎም ሃያ አምስተኛው ዓመት መጣ።

ከሃያ አምስት ዓመታት በላይ መታገሥ ሞኝነት የመሰላት እናታችን ሦራ ፡ ፀሎቷን በራሷ ለመመለስ ብልሃት ያገኘች መሰላት። ታሪኩ እንዲህ ነው:- “ሦራም አብራምን:- እነሆ÷ እንዳልወልድ እግዚአብሔር ዘጋኝ፤ ምናልባት ከእርስዋ (ከባሪያዪቱ ከአጋር) በልጅ እታነጽ እንደ ሆነ ወደ እርስዋ ግባ አለችው። አብራምም የሦራን ቃል ሰማ።”
. (ዘፍጥረት 16÷2-3)

በዚህ “ሦራ ሠራሽ” (ሰው ሠራሽ) አኳኋን የተወለደው ልጅ አብርሃምን እንዲወርስ እግዚአብሔር አልፈቀደም። ዓላማው ስላልነበረ ነው ። በእግዚአብሔር ቃል መሠረት÷ የተስፋው ልጅ ይስሐቅ÷ በተወሰነለት ጊዜ ተወለደ።

በሣራ  ችኮላ የተገኘው ልጅ፡-
እሽማኤል  የተባለው  ሲሆን፥
እርሱም የዛሬዎቹ  የእስራኤል
ጠላቶች የአረቦቹ አባት ነው፡፡
“ዓርብ ዓርብ  ይሸበራል እየሩ
ሳሌም” ይባል  የነበረው፥ ዛሬ
ግን  ዕለት  ዕለት  የሚታየው
ሽብር፡-የሣራ ችኮላ የፈጠረው
የራስን ፀሎት በራስ  የመመለ
ስ ውጤት ነው፡፡   ክርስቲያን
ሆይ!  ሰው ሠራሽ የፀሎት መ
ልስ አንፈልግ፡፡   ብዙ  መዘዝ
ያስከትላል፡፡ ይልቁን፡-  “በፍ
ጹም  ልብህ   በእግዚአብሔር
ታመን  በራስህም   ማስተዋል
አትደገፍ  በመንገድህም  ሁሉ
እርሱን እወቅ፥ እርሱም ጎዳና
ህን ያቀናልሃል” (ምሳሌ 3፥5-
6) ተብሎ እንደ ተጻፈው በመ
ታመን ተስፋችንን እንጠብቅ፡፡

ጌታን ታምኖ መጠባበቅ አ
ያደክምም ማለት አይቻልም፡፡
ነገር ግን እግዚአብሔር፥አምነ
ውት  የሚጠባበቁትን  ሲጥል
ወይም ሲያሳፍር  ታይቶ አይ
ታወቅም፡፡   ይህን  መልዕክት
የምታነቡ፥ጌታን የምትጠብቁ
በት ነገር ይኖራችኋል፡፡  ምና
ልባትም የጥበቃው ዘመን ረዥ
ምና አድካሚ የነበረ ይሆናል፡፡
የሚታየው ሁሉ ጨለማና ለዕ
ምነት  የማይመች  ይሆናል፡፡
ከዚህም የተነሣ አንዳች የዕም
ነት እንቅስቃሴ እንኳ ለማድረ
ግ ጉልበቱ አይኖር ይሆናል፡፡
ነገር ግን  የምናመልከው ጌታ
የአስራኤል ቅዱስ  ማን እንደ
ሆነ  እናስተውል፡፡      በውኑ
ለእግዚአብሔር የሚሳነው  አ
ለን?  ሰማይንና ምድርን፥በው
ስጡ  ያሉትንም፥ ከአለመኖር
ወደ መኖር አላዘዘምን?  ይህን
ንስ ጨለማ፥ ማብራት ይሳነዋ
ልን?  ጌታ ሊያስጠብቅህ ከወ
ደደ  በታማኝነት  ተመችተህ
ጠብቀው፡፡   የዘመኑ መርዘም
አዘናግቶህ፥ተዳክመህ ባለህበት
መልስህ ድንገት እንዳይደርስ
ተጠንቀቅ፡፡  በዕምነት፥ በጽድ
ቅና በድፍረት ወደ ፊት መዘር
ጋት ሲገባህ እንዳትሰንፍ ልብ
ህን አዘጋጅ፡፡  የዮሴፍ የጥበቃ
ሥፍራ (እስር ቤቱ)  መግቢያ
እንደ ነበረው መውጫም የነበ
ረው መሆኑን  አትርሳ፡፡  *
ለአንተም፥ዛሬ ገና ባይገለጥም
ጌታ መውጫን ሳያዘጋጅ  ካለ
ህበት  ሥፍራ እንዳልወሰደህ፥
እንዳልረሳህም ዕወቅ፡፡   ከየት
አንስቶ እዚህ እንደ አደረሰህ
አስብ፡፡ ሰውን መርሳት በሕሪዩ
ስላልሆነ ካለህበት የገባኸው በ
ራስህ ወይም በጠላት ቢሆንም
የማይጥልህን ጌታ፥አምላክህን
እግዚአብሔርን   በትዕግሥት
ብትጠብቅ አታፍርምና አይዞ
ህ! እግዚአብሔርን ተስፋ አድ
ርግ፡፡   በርታና ጽና!   ጌታ
አይዘገይም፡፡     እግዚአብሔር
ይመስገን፡፡  * * * * * * * * *



ፀልዩልን፡፡  ጻፉልን፡፡
ጌታ ይባርካችሁ፡፡

# “ለኢየሩሳሌም ሰላምን ለምኑ”

(መዝሙረ ዳዊት 122 ፥ 6)

የሰው ልጆች ታሪክ፥ ጌታ
እግዚአብሔር በወሰነው ጊዜና
አኳኋን ወደ ፍጻሜ  ሲያዘግም
እየተመለከትን ነው፡፡ ምልክት
ተብለው  በመጽሐፍ ቅዱስ  ከ
ተጠቀሱት  ብዙዎቹ ተፈጽመ
ዋል፡፡  ከምልክቶቹ አንዱ በማ
ቴዎስ ወንጌል  24 ፥ 32 -33
“ምሳሌውንም  ከበለስ  ተማሩ
ጫፍዋ ሲለሰልስ ቅጠልዋም ሲ
ያቈጠቍጥ፥ያን ጊዜ በጋ እንደ
ቀረበ ታውቃላችሁ፤እንዲሁ እ
ናንተ ደግሞ ይህን ሁሉ ስታዩ
በደጅ እንደ ቀረበ እወቁ፡፡”
የሚለው  ነው፡፡  በዚህ  ክፍል
በለስ የተባለላት እስራኤል እን
ደ ሆነች የመጽሐፍ አዋቂዎች
የሚስማሙበት ነው፡፡

እስራኤል በእግዚአብሔር
ቃል መሠረት፡-  ተመልሳ ከተ
መሠረተች   ወዲህ  በተፋጠነ
አኳኋን  በመቋቋም ላይ ናት፡፡
“በዚያም ቀን እንዲህ ይሆናል
ታላቅ መለከት ይነፋል፥ በአሦ
ርም የጠፉ፥ በግብጽ ምድርም
የተሳደዱ ይመጣሉ፥በተቀደሰ
ውም ተራራ በኢየሩሳሌም ለ
እግዚአብሔር ይሰግዳሉ፡፡” (ኢ
ሳይያስ 27፥13)  ተብሎ  የተጻፈ
ው፡-  ወደ  መፈጸም  በድንቅ
እየገሠገሠ  ነው፡፡

እግዚአብሔር     ሕዝቡን
በአሕዛብ መሐከል በበተነ ጊዜ
የጠፋና  የተረሳ   የመሰላቸው
የአሕዛብ መንግሥታት  በዚህ
የእስራኤል   መልሶ   መቋቋም
አልተደሰቱም፡፡  ተቃውሞአቸ
ውም በጽዮን  ግምባታ መጠን
ተፋፍሞአል፡፡  ይህን አስመል
ክቶ በቅርቡ ሾሬሽ የተባለ የደ
ብዳቤ መልዕክት ያወጣውን ጥ
ሪ ባገኘን ጊዜ  ለአንባቢዎቻች
ን ማስተላለፍ  መልካም  ሆኖ
ተሰማን፡፡

“ሾሬሽ”   (ሥረ  መሠረት)
ዓለም አቀፍ  የክርስቲያኖችና
የአይሁድ ኅብረት  የሚባል የ
ድርጅት ደብዳቤ ነው፡፡ ሾሬሽ
ቅጽ 8  ቁጥር   7   (July 2002)
ላይ ፡- በአሜሪካን  የሚኖረው
ሕዝበ ክርስቲያን በሚከተሉት
መንገዶች ለእስራኤል፥ድጋፍ
እና  አንድነቱን እንዲገልጽ፡-
ራባይ (መምሕር) የኺል ኤክ
ስቴይን ጠይቀዋል፡፡ይኸውም
- በፀሎት
(መዝሙረ ዳዊት 122፥6)
- የዕምነታችን  መነሻ  ስለ
ሆነችው እስራኤል በማጥናት፡
- ሐገሪቱን  በመጎብኘት፡-
- በአይሁድና በክርስቲያኖ
ች መሐከል መቀራረብን ለመ
ፍጠር በመተባበር፡-
- አይሁድን  መልሶ በሐ
ገራቸው ለማስፈር በመ
ርዳት ወዘተ፡-

በመጨረሻም፥ከዚህ በታች
በሚገኘው የዌብ አድራሻ
ላይ በመሄድና የድጋፍ
ድምፅ በመስጠት  ከእስራ
ኤል ጋር እንድንተባበር
ጠይቀዋል፡፡ የዌብ አድራሻ
ው እነሆ፡-
www.standforisrael.org



# ውድ ወገኜ፡-

ስለ እግዚአብሔር ፍቅር
አንድ  ጥያቄ   ልጠይቅህ፡፡
ለዚህ  ጥያቄ  የምትሰጠው
መልስ የዘላለም ደስታህንና
ሐዘንህን ይወስናል፡፡ መልስ
ህን  የምታውቁት  አንተና
እግዚአብሔር ብቻ ናችሁ፡፡
ባትመልስም ያው በአንተና
በእግዚአብሔር    መሐከል
ነው፡፡  ጥያቄው  እነሆ፡-
**ድነሃል**?

ይህ ጥያቄ ስለ ጥሩ  ሰ
ውነት አይደለም፡፡  ወይም
ቤተ ክርስቲያን ስለ መሄድ
አይደለም፡፡  የኃጢአት ይ
ቅርታን ስለ መቀበል ነው፡፡
በግልጽ አጠያየቅ፡- የማይቀ
ረው  ሞት፥ ዛሬ ቢመጣብህ
መንግሥተ ሰማይ ትገባለህ ?

ጌታ  እንዲህ  ይላል ፡-
“ሰው ዳግመኛ  ካልተወለደ
በቀር የእግዚአብሔርን መ
ንግሥት ሊያይ አይችልም”
(ዮሐንስ 3፥3)   ይህ  ጌታ
ዳግመኛ መወለድ  ያለው፡-
ሰው  ኃጢአተኛነቱን አም
ኖና ተናዝዞ፥በመስቀል ላይ
በሞተለት  በኢየሱስ አዳኝ
ነት ሲታመን፥የሚቀበለው
ደኅንነት ነው ፡፡    እግዚአ
ብሔር  በመጽሐፍ  ቅዱስ
ውስጥ መዳን የሚቻልበትን
መንገድ ሁሉ  ገልጾልናል፡፡
መንገዱም ከባድ አይደለም
በሥራ ብዛትም አይደለም፡፡
በዕምነት ነው፡፡  እኛ ድነን
አይተነዋል፡፡ አንተም የሚ
ከተለውን የመጽሐፍ ቅዱስ
ዕውነት በመከተል፡-  ዛሬ
መዳን ትችላለህ፥አንችም፡፡

**በ**መጀመሪያ  እግዚአ
ብሔር እንደሚወድህና ለሕ
ይወትህ  ዓላማ  እንዳለው
ተረዳ፡- መጽሐፍ እንዲህ ይላል

“በእርሱ   የሚያምን  ሁሉ
የዘላለም  ሕይወት  እንዲኖ
ረው   እንጂ    እንዳይጠፋ
እግዚአብሔር አንድያ ልጁ
ን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን
እንዲሁ ወዶአልና፡፡”
(የዮሐ ንስ ወንጌል 3 ፥ 16)

**ኃ**ጢአተኛ መሆንህን
ተረዳ፡-

“ሁሉ ኃጢአትን ሠርተዋል
ና የእግዚአብሔርም ክብር
ጐድሎአቸዋል፤”
(ወደ ሮሜ ሰዎች 3 ፥ 23)

**ኃ**ጢአተኛ ሁሉ ሞት ይጠ
ብቀዋል፡-

“የኃጢአት ደመወዝ ሞት
ነውና የእግዚአብሔር የጸጋ
ስጦታ  ግን በክርስቶስ ኢየ
ሱስ በጌታችን  የዘላለም ሕ
ይወት ነው፡፡”
(ወደ ሮሜ ሰዎች  6 ፥ 23)

“ለሰዎችም  አንድ  ጊዜ
መሞት ከእርሱ  በኋላም ፍ
ርድ  እንደ  ተመደበላቸው
እንዲሁ  ክርስቶስ  ደግሞ፥
የብዙዎችን ኃጢአት ሊሸከ
ም አንድ ጊዜ  ከተሰዋ በኋ
ላ፥ያድናቸው ዘንድ ለሚጠ
ባበቁት  ሁለተኛ ጊዜ  ያለ
ኃጢአት ይታይላቸዋል፡፡”
(ዕብራውያን  9 ፥ 27 - 28)

**የ**ኃጢአታችን ዕዳ ተከ
ፍሏል፡፡

---

“እኛ     በእርሱ    ሆነን
የእግዚአብሔር  ጽድቅ እን
ሆን ዘንድ ኃጢአት ያላወቀ
ውን እርሱን (ክርስቶስን) ስ
ለ እኛ ኃጢአት አደረገው”
(ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች 5፥21)

**ስ**ለ ሰው  ኃጢአት  የሞተ
ኢየሱስ ብቻ  ስለ ሆነ  ያለ
እርሱ መዳን የሚችል ማን
ም የለም፡፡

“እኔ መንገድና  ዕውነት ሕ
ይወትም  ነኝ ፡ በእኔ  በቀር
ወደ አብ የሚመጣ የለም፡፡”
(የዮሐንስ ወንጌል  14 ፥ 6)

**ዕምነት፡-** ይህን እናስ
ተውል፡፡  ኢየሱስን  አምኖ
መቀበል ማለት እርሱ  ያስ
ተማረውን ትምሕርት መከ
ተል ማለት ነው፡፡   ስለዚህ
ልባዊም፥አፋዊም፥ ተግባራ
ዊም ነው፡፡  የልጅነትን ሥ
ልጣን ሲቀበሉት የሚታወ
ቀው በዚህ ምክንያት ነው፡፡

---

“ለተቀበሉት ሁሉ ግን፥በስሙ
ለሚያምኑት ለእነርሱ  የእግዚአ
ብሔር  ልጆች  ይሆኑ  ዘንድ
ሥልጣንን ሰጣቸው፤”
(የዮሐንስ ወንጌል  1 ፥ 12)

---

ውድ ወገኔ፡- ደኅንነት የሚ
ታወቅ ነው፡፡ በመጽሐፍ ቅ
ዱስ ውስጥ ጌታ ገልጾታል፤
ስለዚህ ዕመንና ዳን፡፡ መንግ
ሥተ ሰማይ ቀርባለችና፡፡

# ፀሎት

እግዚአብሔር ሆይ፡-  እኔን
ኃጢአተኛውን ማረኝ፡፡ ስለ
ኃጢአታችን  ሞቶ  ከሞት
ባስነሣኸው  በየሱስ አምናለ
ሁ፡፡  ከዛሬ ጀምሮ ትምሕር
ቱን በመከተል  እኖራለሁ፡፡
ከክፉ መንገዴም  እመለሳለ
ሁ፡፡ አንተም በመንግሥትህ
ተቀበለኝ ፡፡     ስለ   ቅዱስ
ልጅህ  ስለ ኢየሱስ  ስትል
ፀሎቴን ስማኝ፡፡  አሜን፡፡

(አድራሻችን  በመግቢያው  ላይ
ይገኛል፡፡)   ኢየሱስ ጌታ ነው፡፡
.              ጌታ ይባርክህ፡፡